# *የወያኔና መጅሊስ ሴራ በሀጅ የፀሎት ስርዐት*

ወያኔ ጠንካራ ሀይማኖታዊ ይዘታችን በማፈራረስ፤ደካማ ኢስላምን ለመቅረፅ ከልቡ መስራት ከበረታበት ጊዜ ጀምሮ፤በሙስሊሙ ወገን የተከሰቱና ቀጣይነት ሊኖራቸው የሚገባ መልካም እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡

ከጠበበ ብሄርተኛነት ፈንጠር ብሎ በህብረት ስለ ኢስላም ማሰብ፤ወያኔ ለኢስላም ሁነኛ ጠላትነቱን መረዳት፤ቀላል የአመለካከት ልዩነቶች የፈጠሩትን ፊርቃ ቸል በማለት ጠላትን በጋራ ለመፋለም መነሳሳት፤በወያኔና መጅሊስ እየተሰራበት ስላለው ሴራ በፈጠነ ሁኔታ መረጃ መለዋወጥና የመሳሰሉት ከነዚህ አበረታች ጅምሮች የሚታሰቡ ናቸው፡፡በተለይም ሀገር ውስጥ ያሉ ወንድሞቻችን እየፈፀሙት የሚገኙት አኩሪ ተግባር ሰሞነኛ እንዳይሆን የዱዐ እርዳታ ይፈልጋል፡፡

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢዎች ሀረማያ ዩንቨርሲቲና ተከትሎ በመስከረም የመጀመሪያ ሳምንት በመላ ሀገሪቱ የተካሄደው በ‹‹አህባሽ›› የማጥመቅ ዘመቻ፤ኮርሱ ይሰጥባቸው የነበሩ ማዕከሎች ሁሉ በወያኔ የፀጥታ ሀይሎች ምን ያህል እንደታጠሩ ያውቃሉ፡፡ያም ሆኖ ከደህንነታቸው ይልቅ ለኢስላም ቅድሚያ በሰጡ ጀግና ወንድሞቻችን አማካይነት የመረጃ ዝርፍያ ሲካሄድ ነበር፡፡ከበቂ በላይ የድምፅ፣የምስል መረጃዎች ከወያኔ የደህንነት ሰራተኞች አይን ስር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አላሁ አክበር!

ለደህንነት ሲባል መገለፅ ባይገባው እንጂ፤እጅግ አስቂኝና የማይገመት በሆነ መልኩ መረጃ እየተሰበሰበ ሲቀባበል ነበር፡፡ይህን ሲያከናውኑ ከነበሩ ወንድሞች አንዱ እንዳስቀመጠልን ‹‹ወያኔ ለኛ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት ስራዎቻችን እንዲሳኩ ረድቶናል›› ብሎናል፡፡-‹‹ብልጥን አላህ ይበልጠዋል!››

በነዚህ የመረጃ ትግሎች፤አንድ ወንድም ቦሌ አየር መንገድ ላይ ሲፈተሽ ተይዞበት የነበረውን ጠቃሚ መረጃ እና ራሱን ለማዳን ተንቀሳቃሽ ስልኩን (አይ ፎን) በጉቦ ከመስጠቱ ባሻገር የደረሰ አደጋ የለም፡፡-አልሀምዱሊላህ!

የሀገር፣የፖለቲካ ቡድን፣የተቃዋሚ አንጃም ይሁን ሌላ ስብስብ ጥንካሬ ከሚለካባቸው ሚዛኖች አንዱ ጠንካራ የመረጃ ሴል መሆኑ እርግጥ እንደመሆኑ መልካም እዝ ያለው፣ታማኝ፣ታታሪና ደፋር የመረጃ ማዕከል ያስፈልገናል፡፡ለነገው እኛነታችን የታሪክ ጎርፍ የተፋው ደለል ላለመሆን በዚህች ሀገር ከይስሙላ የዘለለ ቦታ ያሻናል!እያለን እንደሌለን የምንቆጠርባቸው ዘመን ሊያበቃ ይገባል! ይህን የምንጎናፀፈው ደግሞ በምኞት አይደለም!ከውጭ በምዕራባውያን፤ከውስጥ በፅንፈኛ የማህበረ-ቅዱሳን አባላት፣በቅርቡ የፌዴራል መንግስቱ የስልጣን ባጥ ላይ እየተመሙ ያሉ ፕሮቴስታንቶች፣የኦርቶዶክስ ቤተ-ክህነት ህልመኞችና የመሳሰሉት ከሚያደርጉበት ጫና ራሱን የመታደግ አቅም የሌለው ወያኔ ጡንቻችንን አፈርጥመን ስንቀርብ ብቻ ነው ድምፃችን ሊያዳምጥ ፈቃደኛ የሚሆነው!

ኢትዮጵያ ውስጥ በሙስሊሙ ላይ አሁን እየተፈፀመ ያለው በደል የሚቆም አይደለም፡፡ይህን ማስቆም የምንችለው በአላህ እርዳታ እኛ ብቻ ነን!ስለ አለፉት አስራ አራት የስቃይ ክፍለ-ዘመናት እየዘከርን፤አሁን መክፈል የሚገባን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍለን ‘በደል በቃን’ ካላልን ዝንተ-ዐለም እየተረገጥን እንኖራለን!ነፃነት እንደስጦታ የሚታደሉት አይደለም…ሊከፈልለት

የሚገባ መስዋዕትነት አለ፡፡ያን መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁና እየከፈሉ ያሉ ጠንካራ ወንድሞቻችን አሉ!አላህ ይጠብቃቸውና!ሆኖም የነሱ ቤዛነት ብቻውን በቂ አይደለም፤ የእያንዳንዳችን አስተዋፅዖ ይፈልጋል፡፡

የወያኔ ቅጥቀጥ ከሆነው አሻንጉሊቱ 'መጅሊስ' ፅህፈት ቤት አንስቶ አስፈላጊ በተሰኙ ጥጎች ሁሉ የተዘረጋ የስለላ መረብ መኖሩንና አስገራሚ መረጃዎችን 'መዝረፍ' እንደተቻለ መደበቅ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ነገር ግን ይህ ቢታወቅ ወያኔ ሊዘጋ የሚችለው በር እንደሌለ እርግጠኞች ስለሆንን 'ከመጅሊስ' ጉደኞች ሻንጣ የተፈለቀቀች የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ያዘለችውን ሚስጥር ልናካፍላችሁና አስቸኳይ መፍትሄ በጋራ እንድንፈልግ መረጥን፡፡

ጉዳዩ የ1432 አመተ-ሂጅራ የሀጅን ፀሎት ጉዞ መሰረት ያደረገ ነው፡፡የወያኔ አሳላፊ በሆኑ 'መጅሊሰኞች' ችሮታ 'መንግስት' ለ‹‹አህባሽ›› አጠቃላይ እንቅስቃሴ እስካሁን ያወጣው ወጪ ከዘንድሮው የሀጅ ስነ-ፀሎት ተጓዥ ምዕመናን ገቢ ከመጅሊሱ (ከህዝበ-ሙስሊሙ ካዝና) ተቀንሶ (ተነጥቆ) 'ለመንግስት' ገቢ እንዲደረግ ተወስኗል!?¡

ምን አይነት ስሜት እንደተሰማችሁ መገመት ይቻላል፡፡'ንቀቱ በዛና፤ሰፈርኩሽ በቁና' ይሏል ይህም አይደል?!

ሌላኛው ሚስጥራዊ ሴራ.....

ሳዑዲ አረቢያን በቀንደኛ አሸባሪነትና ወሀብይነት ሲያወግዙ ከከረሙት ሰዎች መካከል የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ሰብሳቢ የሚሰኘው ሸህ አህመዲን አብዱላሂና የመጅሊሱ ዋና ፀሀፊ የሆነው ግለሰብን ጨምሮ በርካታ የወያኔ ምንደኞች ወደ 'አሸባሪዋ' ሀገር ሊመጡ ነው፡፡በየአመቱ እንደተለመደው ለእያንዳንዳቸው በቀን 125 ዶላር የውሎ አበል እየተቆረጠላቸው እያስጠቁት በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ስም የሚቀናጡበት 'ሽርሽራቸው' ዘንድሮ የተለየ አጀንዳ ተይዞለታል፡፡ከዚህ በታች በቅደም ተከተል የተተነተኑት ተወያይተን ልንወስንባቸው የሚገዱን ናቸው፡፡

1-ከዚህ ቀደም ባልተፈፀመ መልኩ ፤አስር የመንግስት ደህንነት ሰራተኞች በመጅሊሱ ማህተም የሙስሊምነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷቸው (ሙስሊሞች ላይሆኑ ይችላሉ)፤አዲስ አበባ ከሚገኘው የሳዑዲ ኤምባሲ መግቢያ ቪዛ እንዲያገኙና ከመጅሊሱ ባለስልጣናት ጋር ወደ ሳዑዲ አረቢያ ከበረሩ በኋላ፤የተቀደሱት መካና መዲና ከተማ ብቻ ሳይሆን 'ሸሆቹ' ሊመሩት በታቀዱት የማደናገሪያ ስብሰባዎች አስፈላጊውን ሚና እንዲጫወቱ፤

2-ኢትዮጵያውያን የሀጅ ፀሎተኞች አረፋ፣ሚና፣መካና መዲና ፀሎታቸውን በሚያካሂዱበት፣ በሚያርፉበት ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ ‹‹የአህባሽ›› አመለካከት እንዲሰርፅባቸውና አህለል ሱና ወልጀመዐ-ሳዑዲ አረቢያን እንዲጠሉ፤በዚህ የተካኑ ‹‹የአህባሽ›› ዲስኩረኞችን በመጅሊሱ ወጪ ከኢትዮጵያ ወደሳዑዲ አረቢያ መውሰድ፤፤ ከዚህ ቀደም ይደረግ እንደነበረው በማንኛውም 'የውጭ' አሊም (አህባሽን ተቃዋሚ) ትምህርት እንዳይሰጥ፤

3-ጅዳ ከተማ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ፅ/ቤት ሚስጥራዊ አቀናጅነት፤በቅርቡ የተከበረችው መዲና ከተማ አንዳንድ አንካሳ አመለካከት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ‹‹አህባሽን›› ለማንሰራፋት ድብቅ ስብሰባ አካሂደው ነበር፡፡የመጅሊስ ባለስልጣናት(ምስለኔዎች) በተገኙበት ይህን የሚያጠናክር ሌላ ስብሰባ እንዲካሄድ፤ለዚህም አስፈላጊው ቅድመ-ሁኔታ ለማስተካከል ሳዑዲ

አረቢያ ውስጥ የሚገኙ 'የመጅሊሱ' ቅጥረኞች ከኤምባሲና ቆንስላ ፅህፈት ቤቱ በመተባበር እንዲሰሩ፤

4-ከሀጅ ፀሎት ፍፃሜ በኂላ፤መካ፣መዲና፣ሪያድ፣ጅዳና ጣይፍ ከተማ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን 'ሀገራችን ውስጥ በሀይማኖት ስም ሽብር የሚያካሒዱ ወገኖችን ለመዋጋት' በሚል ማደናገርያ ርዕስ 'ከመጅሊሱ' ተወካዮች ገለፃ እንዲሰጥ፤በየከተማው በተለይ ሪያድ የሚገኘው ኤምባሲና ጅዳ ቆንስላ ፅህፈት ቤት የተሰባሳቢውን አመለካከት ለማዛባት ከ'ወሀቢይ' ጋር ተቃርኖ ያላቸው ሀሳቦች እንዳይንፀባረቁ ጥንቃቄ መውሰድ፤ትግሉ ከአሸባሪዎች እንጂ ከየትኛውም እስላማዊ አመለካከት ጋር እንዳልሆነ ለመሳልና ለማሳመን መጣር፤፤

ከላይ እንደተቀመጠው ከድፍረት የተሻገረ፤አቂዳችን ለማፍረስ አሉታዊ እንድምታ ያለው ሴራ መጅሊሱን በተቆጣጠሩ የወያኔ ሹመኞች ተወስኗል፡፡እነዚህን ጥቃቶች ለመከላከል ከዚህ የሚከተሉትን መፈፀም ከኛ ይጠበቃል፡፡

1-በዘንድሮው የ1432 አመተ-ሂጅራ የሀጅ ፀሎት ለመፈፀም ለሚጓዙ ወገኖቻችን መጅሊሱ ከመንግስት በመተባበር ስለሚሰራው ደባና በተለይ ከሀጅ ኢባዳ ያልተያያዘ ትምህርት ስለሚሰጣቸው ጥንቃቄ እንዲወስዱ መምከር፤

2-በተለያዩ የሀጅ ፀሎት አመታት አስተማሪ የሌለው ወገናቸውን ያለምንም ክፍያ ትምህርት ሲሰጡ የነበሩ ወንድሞች መጅሊሱ ይህን ቢያግዳቸውም፤መጅሊሱ በማይቆጣጠራቸው በርካታ ቦታዎች ሁጃጁን በመሰብሰብ ማንቃት፣ማስተማር፤ስለአህባሽ አደገኛነትና ስለወያኔ መንግስት ፀረ-ኢስላም አፍራሽ ድርጊት ማስገንዘብ

3-የመጅሊሱ ባለስልጣናት በሚያርፉባቸው ሆቴሎችና ድንኳኖች በመገኘት፤ምድራዊ ህይወታቸውን ለማሳመር ከወያኔ በማበር ዲናቸውን ማፍረሳቸውና አኼራቸውን ማበላሸታቸው አግባብ እንዳልሆነ ማስታወስና ድርጊታቸውን በአፅንዖት ማውገዝ፤

4-ከሀጅ ፀሎት በኂላ መጅሊሱ በተለያዩ የሳዑዲ አረቢያ ከተሞች ለኢትዮጵያዊው ሙስሊም ነዋሪ ሊያካሂድ በነደፈው ስብሰባ ሁሉም በመገኘት ድርጊታቸውን መቃወም፤በሚቀርቡለት የማታለያ ዲስኩሮች ሳይታለል መጅሊሱ ህዝበ-ሙስሊሙ ያልመረጠው፣ሙስሊሙን የመምራት ብቃት የሌለው የዲን ጠላቶች ስብስብ መሆኑን በድፍረት ማስቀመጥ ያሻል፡፡

በዚህ ረገድ ነዋሪነታችሁ ሳዑዲ አረቢያ በተለይ የተጠቀሱት ከተማዎች የሆናችሁ ወንድሞች ቅድመ-ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባችኂል፡፡ከሌላው አለም ለሀጅ ፀሎት ወደ ሳዑዲያ የምትጓዙ ወገኖችም ድርሻችሁ የሚናቅ አይደለም፡፡ይህ ፅሁፍ ከተበተነ ወዲህ ወያኔና መጅሊሱ እስትራቴጂያቸውን ቀይረው ስብሰባዎችን ቢሰርዙ እንኳ የመጅሊስ ባለስልጣናትን ባሉበት አድናችሁ ነውራቸውን ልትግቷቸው ይገባል፡፡ከነሱ ቀደም የነበሩ ቢጤዎቻቸው ሁሉ ወያኔ እንደ ሸንኮራ መጥጦና ለሚፈልገው ስራ ተጠቅሞባቸው እንደተፋቸው በወጉ አስገንዝቧቸው፡፡ ሀቅን ተናገሯት…አትፍሩ…ኢንሻ አላህ መጨረሻ ድሉ የኛ ነው !!!!!

ይህን ፅሁፍ በኢ-ሜይል ብቻ ሳይሆን ሀርድ ኮፒውን አባዝቶ በማከፋፈል ኢስላማዊ ግዴታዎን ይወጡ!

መልዕክትዎ ይጠቅመናል Strongmuscle61@yahoo.com